# የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ የ2017 በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት

# እና

# የ2018 በጀት ዓመት የስራ ዕቅድ

ጥቅምት 23/2018

ባህር ዳር /ኢትዮጵያ

ክቡራትና ክቡራን የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ ባለአክሲዮኖች!

ከሁሉ አስቀድሜ ለጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ 3ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንኳን በሰላም አደረሳችሁ!! ጥሪያችንን አክብራችሁ በዚህ ጉባኤ የተገኛችሁ ውድ ባለአክሲዮኖች፣ በራሴ፣ በቦርዱ፣ በማኔጅመንቱ እና በአጠቃላይ ሰራተኞች ስም የከበረ ሰላምታዬን ላቀርብላችሁ እወዳለሁ።

1. መግቢያ

የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች፣

ሀገራችን ኢትዮጵያ የህብረተሰቡን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማጎልበት፣ የፋይናንስ ተደራሽነትንና አካታችነትን ለማስፋፋት የተለያዩ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች። የፋይናንስ ሴክተሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ (NBE) የበላይ ተቆጣጣሪነት የሚመራ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በስሩ 32 ባንኮች (2 የመንግስትና 30 የግል)፣ 18 የመድህን ሰጪ ኩባንያዎች (1 የመንግስት እና 17 የግል)፣ 56 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት (9 መንግስታዊ፣ 16 መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደገፉ እና 31 የግል ማይክሮ ፋይናንሶች)፣ 6 የመንግስት የሊዝ ኩባንያዎች፣ 91 ገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች፣ 18 የክፍያ መሳሪያ ሰጭዎች/የስርዓት ኦፕሬተሮች/፣ 1 ድጋሜ ኢንሹራንስ 13 የውጭ ምንዛሬ ቢሮዎች ፣ እና 4 የካፒታል ገበያ አገለግሎት ሰጭ ድርጅቶች ይገኛሉ።

የፋይናንስ አሰራሩን ለማዘመን እና ተደራሽነቱን ለማስፋት የውጭ ባንኮች ወደ ገበያ እንዲቀላቀሉ በር የተከፈተ ሲሆን፣ ይህም የባንኮችን ቁጥር ከፍ ከማድረጉም ባሻገር በባንኮች መካከል የተወዳዳሪነትን መንፈስ የሚያጎለብት እና ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት የተቀላጠፈ እንደሚያደርግ ይታመናል። እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በፋይናንስ ኢንዱስትሪው ላይ መሻሻል እንደሚያመጣ ይታመናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ድረ-ገጽ እንደሚያሳየው እ.ኢ.አ እስከ ሰኔ 30/2017 በአጠቃላይ በሀገራችን አነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ብዛት 56 ሲሆኑ፣ እነዚህ ተቋማት ያስመዘገቡት ካፒታል ብር 11.4 ቢሊየን መድረሱን ያሳያል። በተጨማሪም ሌሎች 54 ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በምስረታ ሂደት ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል።

በ56ቱ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት በከተማና በገጠር በድምሩ 1,138 ቅርንጫፎች ተከፍተው ለህብረተሰቡ የቁጠባና ብድር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከብሔራዊ ባንክ ፋይናንሻል ስታቢሊቲ ሪፖርት ምንጭ ለመረዳት እንደተቻለው፣ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጠቅላላ ሀብት መጠን ብር 60.1 ቢሊዮን የደረሰ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ ተጨማሪም 829 ሺህ የብድር ደንበኞች በድምሩ ብር 39.7 ቢሊየን ከተቋማቱ የብድር ተጠቃሚ መሆናቸውን ሪፖርቱ ያመለክታል። ተቋማቱ ቁጠባ በማሰባሰብ ረገድም ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኙ

ሲሆን፣ እስከ ተጠቀሰው ጊዜ ድረስ የተሰበሰበው የቁጠባ መጠን ብር 31.4 ቢሊዮን እንደደረሰ እና የደንበኞች ቁጥር 5.6 ሚሊየን መድረሱን ሪፖርቱ ያመለክታል።

## 2. የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ. አፈጻጸም ሪፖርት

**የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች፣ ክቡራትና ክቡራን፤**

ከዚህ በመቀጠል የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ የ2017 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2018 በጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ተቋማችን ሥራ ከጀመረበት ባለፉት ሦስት ዓመታት በክልሉ ባጋጠሙ የጸጥታ ችግር ምክንያት ከፍተኛ ተግዳሮት ያጋጠመው ቢሆንም፣ በቦርዱ፣ በማኔጅመንቱ እና በሰራተኞቹ እንዲሁም በባለአክሲዮኖች ባልተቋረጠ ጥረት የተቋሙ ህልውና አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ማድረግ ተችሏል።

ይህ ሪፖርት የ2017 በጀት ዓመት የኩባንያውን የሥራ እንቅስቃሴ ማሳየት እንደመሆኑ መጠን፣ ከእቅድ እና ካለፈው ዓመት አፈጻጸም ጋር በማነጻጸር፣ አለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ስታንዳርድን (IFRS) መሰረት አድርጎ ተዘጋጅቷል። በዚህም መሰረት የተቋማችንን የ2017 በጀት ዓመት በኦፐሬሽን እና በፋይናንስ የስራ ዘርፎች የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ከእቅድ ጋር በማነጻጸር እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

### 2.1. የኦፐሬሽን ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም

#### 2.1.1. የቁጠባ ሥራ እንቅስቃሴ አፈፃፀም

የተቋሙን የገንዘብ አቅም ለማጠናከር እና ለህብረተሰቡ የብድር አገልግሎት በስፋት ለማዳረስ ከብድር ደንበኞችና የብድር ደንበኛ ካልሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መጠነ ሰፊ ቁጠባ መሰብሰብ የግድ ነው። ስለሆነም በበጀት ዓመቱ ማኔጅመንቱና ሰራተኛው ቁጠባን በስፋት ለመሰብሰብ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

- በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ለመድረስ የታቀደው አጠቃላይ የቁጠባ መጠን 128,279,389.02 ብር ሲሆን፣ የአመቱ አፈፃፀም ብር 161,238,037.96 መድረስ ተችሏል። ይህም የዓመቱን የእቅድ ክንውን አፈፃፀም ሲታይ በ125% ማሳካት ተችሏል። ይህ አፈጻጸም አሁን በክልሉ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ የላቀ አፈጻጸም እንደሆነ ያሳያል።

#### 2.1.2. የብድር ዕቅድ አፈፃፀም

ከቁጠባ አገልግሎት ቀጥሎ የፋይናንስ ተቋማት ለደንበኞች ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች መካከል አንዱ የብድር አገልግሎት ነው። በመሆኑም ጥራት ያለው የብድር አገልግሎት ለህብረተሰቡ በስፋት በማቅረብ ከብድር የሚገኘውን የተቋሙን የገቢ ምንጭ ከማሳደጉም በላይ ቁጠባ ለመሰብሰብ በር ከፋች መንገድ ነው። ስለሆነም የብድር አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም በብድር ስርጭት፣ በብድር አሰባሰብ፣ እና በተበዳሪዎች እጅ ላይ የሚኖረውን የብድር መጠን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ የተሻለ ሥራ ተሰርቷል። በዚሁ መሰረት የበጀት ዓመቱ የብድር ሥራ እቅድ

አፈፃፀምና የተገኘው ውጤት ካለፈው ተመሳሳይ የበጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር እንደሚከተለው ቀርቧል።

- በ2017 በጀት ዓመት ጠቅላላ ሊሰራጭ የታቀደው የብድር መጠን 233,206,624.00 ብር ሲሆን፣ የተሰራጨው የብድር መጠን ብር 218,746,329.34 ነው። ይህም በበጀት ዓመቱ 93.4% ሲሆን፣ ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወቅት ከተሠራጨ የብድር መጠን ብር 71,252,855.92 ጋር ሲነፃፀር የብር 147,493,473.42 ብልጫ አለው።
- በበጀት ዓመቱ ጠቅላላ ሊሰበሰብ የታቀደው የብድር ተመላሽ መጠን ብር 83,260,095.32 ሲሆን፣ የተሰበሰበው የብድር አፈፃጸም መጠን ብር 84,936,761.23 (102%) ነዉ።
- በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በተበዳሪዎች እጅ ይኖራል ተብሎ የታቀደው የብድር መጠን 251,703,072.00 ብር ሲሆን፣ ክንውኑ ብር 235,588,548 ነው። ይህም በበጀት ዓመቱ ማሳካት የተቻለው የእቅዱን 93% ሲሆን፣ ካለፈው ተመሳሳይ በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረው የብድር መጠን ከብር 104,355,579.41 ጋር ሲነፃፀር የብር 131,232,969.00 ብልጫ አለው።
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ከ90 ቀን በላይ ሳይከፈል የቆየ ውዝፍ ውስጥ የገባ ብድር መጠን ብር 2,931,718.82 ሲሆን፣ የተቋሙ ውዝፍ ውስጥ የገባ ብድር ምጣኔ 1.25% ነው። ይህም ብሔራዊ ባንክ ካስቀመጠው 5% ዝቅተኛ መመዘኛ በታች መሆኑን ያሳያል። ይህ እንዲሆን ብድር በማስመለስ ሂደት ውስጥ ሰራተኛው ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን አንዱ ማሳያ ነው።

### 2.1.3. አዲስ ቅርንጫፎችን መክፈት

ቅርንጫፎች ተቋሙንና የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን አገናኝ ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው። ስለሆነም የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋት በየጊዜው የአዋጪነት ጥናት እየተደረገ የቅርንጫፎችን ቁጥር መጨመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል። ስለሆነም አሁን በክልሉ ባጋጠመው ተደጋጋሚ የጸጥታ ችግር እና የገንዘብ እጥረት ምክንያት አራት ቅርንጫችን ለመክፈት ታቅዶ ሁለት ቅርንጫፎች (50%) እንዲከፈቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ተቋሙ አሁን ያሉት ቅርንጫፎች ብዛት ዘጠኝ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ ጎንደር እና እንጂባራ ከተማ ቅርንጫፎችን በአዲስ የተከፈቱትን ያካትታል።

## 2.2. የፋይናንስ ዘርፍ ዕቅድ አፈፃፀም

### 2.2.1. ሀብት

የኩባንያው አጠቃላይ ያለው የሀብት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማደግ ላይ ይገኛል።

- በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የተቋሙ የሀብት መጠን ብር 278,325,080 ነው። ይህም ባለፈው ዓመት ከነበረው ብር 131,207,796.01 ጋር ሲነፃፀር በብር 147,117,283.82 ብልጫ አለው።ይህ የተቋሙ እድገት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ተቋሙ አጠቃላይ ካለው

ሀብት ውስጥ የ84% ድርሻውን የሚይዘው ከብድር የሚሰበሰብ ሀብት በመሆኑ፣ ገቢ ሊያስገኝ የሚችል የሀብት መጠን አሁንም ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል። በመሆኑም ይህ ተቋሙ ጤናማ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ያሳያል።

### 2.2.2. እዳ

ተቋሙ ሥራን ለማስፋፋት ከፍተኛ እገዛ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ ቁጠባ ነው። በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ ብር 163,292,272 ቁጠባ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ሌሎች የአጭር ጌዜ ተከፋይ ሂሳብ ብር 7,733,175 በአጠቃላይ የተቋሙ እዳ ብር 171,025,447 ሆኖ ተመዝግቧል:: በተጨማሪም ከተለያዩ ባንኮች ብድር ለማግኘት የተሞከረ ቢሆንም፣ በተለያዩ ምክንያቶች ብድር ማግኘት አልተቻለም። ይህ ደግሞ በብድር ስርጭት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ለመፍጠር ችሏል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በያዝነው በጀት ዓመት ተቋሙ ከባንኮች የተሻለ ብድር ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

### 2.2.3. ካፒታል

በ2016 ዓ.ም ጥቅምት ወር በተካሄደው 1ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ የተቋሙን የአክሲዮን ካፒታል ወደ ብር 500 ሚሊየን ለማሳደግ የሚያስችል ስትራቴጂያዊ ውሳኔ የተላለፈ ሲሆን፣ የጉባኤው ቃለ-ጉባኤ በብሔራዊ ባንክ መጽደቁን ተከትሎ ወደ ተግባር መግባቱ ይታወሳል::ይህንኑ መነሻ በማድረግ፣ እስከ አመቱ መጨረሻ ድረስ የተቋሙ ካፒታል ከመነሻ ካፒታል ብር 54,110,000 ወደ ብር 80,770,000 ማሳደግ ተችሏል:: በተጨማሪም በዚህ ዓመት ለነባር 774 ባለአክሲዮኖች 1,187 አክሲዮን ብር 5,935,000 እና ለ57 አዲስ ባለአክሲዮኖች 588 አክሲዮኖችን ብር 2,940,000 በመሸጥ በድምሩ 1,775 ተጨማሪ አክሲዮኖች መሸጥ የተቻለ ሲሆን፣ህጋዊ መጠባበቂያ እና የተጠራቀመ ትርፍን ጨምሮ የተቋሙ ጠቅላላ ካፒታል ወደ ብር 107,299,633 አድጓል:: የባለአክሲዮኖች ቁጥርም ከ2550 ወደ 2,683 አድጓል::

### 2.2.4. ገቢ

ጣና ማይክሮ ፋይናንስ የፋይናንስ ተቋም እንደመሆኑ መጠን፣ የአክሲዮን ማህበሩ ዋነኛው የገቢ ምንጭ ከብድር የሚሰበሰብ ወለድ ሲሆን፣ ተጨማሪ የገቢ ምንጮች ደግሞ የአገልግሎት ክፍያ፣ የብድር ኢንሹራንስ፣ ከባንክ ተቀማጭ የሚገኝ ወለድና ሌሎች ናቸው። በመሆኑም በያዝነው የበጀት ዓመት የተሰበሰበው ጠቅላላ የገቢ መጠን ብር 45,377,650 ሲሆን፣ ይህም በበጀት ዓመት ውስጥ ለመሰብሰብ ከታቀደው የገቢ መጠን ከብር 53,583,801 ጋር ሲነፃፀር ክንውኑ 85% ነው። ይህ የሚያሳየው ተቋሙ በአመቱ ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥም ሆኖ የተሻለ ተግባር ያከናወነ መሆኑን ነው።

### 2.2.5. ወጪ

በ2017 በጀት ዓመት ለሰራተኞች ደመወዝ፣ ለየቅርንጫፎች ቢሮ ኪራይ፣ ለቁጠባ ወለድ፣ ለኮር ባንኪንግ አገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ለሌሎች አስተዳደራዊ እና ለኦፕሬሽን ተግባራት ብር

36,054,487 ወጪ ለማድረግ የታቀደ ሲሆን፣ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የተመዘገበው አጠቃላይ የወጪ መጠን ብር 28,868,899.00 ነው። ይህ ከታቀደው ወጪ 80% ያህል ወጪ እንደተመዘገበ የሂሳብ መዝገቡ ያሳያል። በመሆኑም ከተመዘገቡት ወጪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት የሰራተኛ ደመወዝ ወጪ፣ የቁጠባ ወለድ ወጪ፣ የቢሮ ኪራይ ወጪ እና ቋሚ ዕቃዎች እርጅና ቅናሽ ወጪዎች ናቸው።

#### 2.2.6. ትርፍ

በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ ብር 15,711,114 ከታክስ በፊት ለማትረፍ ታቅዶ ብር 16,508,751 ማትረፍ ተችሏል። ይህም የበጀት ዓመቱ የእቅድ ክንውን አፈፃፀም ሲታይ 105% ማሳካት የተቻለ ሲሆን፣ በወቅቱ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሲታይ እጅግ በጣም አመርቂ አፈፃፀም ነው ብለን እናምናለን።

#### 2.2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጨማሪ የሥራ እንቅስቃሴ

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ መደበኛ፣ አስቸኳይ እና የንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በማካሄድ ቀጥሎ የተመለከቱትን አበይት ተግባራት አከናውኗል፡-

- የተቋሙን የሥራ አፈፃፀም በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ እና በዓመት መጨረሻ በመገምገም አስፈላጊ ውሳኔዎችን አሳልፏል።
- የተቋሙን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት መርምሮ አጽድቋል።
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን እንዲላክ አጽድቋል።
- የብድር ወለድ ምጣኔ እና የቁጠባ ወለድ ምጣኔ ማሻሻያዎችን አጽድቋል።
- ተቋሙ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት የተሻለ እንዲሆን ከተቋሙ ማኔጅመንት ጋር አብሮ እቅዶችን በማውጣት አከናውኗል።
- የተቋሙ የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ ከስራ አመራር ቦርዱ በተሰየመ የባለሙያ ቡድን እንደገና እንዲረቀቅና አዲሱ የንግድ ሕግ በሚያዝዘዉ መሠረት የቀድሞዉ መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ በማዋሃድ እንዲዘጋጅ ያደረገ ሲሆን የተዋሃደዉ ረቂቅ ሰነድ ለሁለተኛ አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጸድቅ አዘጋጅቶ አቅርቧል፡፡

### 2.3. በሥራ ላይ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እና የመፍትሄ ሃሳቦች

#### 2.3.1. ያጋጠሙ ችግሮች

በበጀት ዓመቱ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ችግሮች አጋጥመዋል፡-

- በክልሉ ያጋጠመው የጸጥታ ችግር የንግድ እንቅስቃሴው እንዲቀዛቀዝ በማድረጉ ምክንያት በቁጠባ እና ብድር እንቅስቃሴው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል።
- በሀገሪቱ ባጋጠመው የገንዘብ ግሽበት ምክንያት ለብድር እና ለተለያዩ እንቅስቃሴዎች የሚውል የገንዘብ እጥረት መከሰቱ ስራችን አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎታል።
- የአክሲዮን ሽያጭ በነባርም ሆነ በአዲስ ባለ አክሲዮኖች በተፈለገው መጠን አለመከናወን

- የተለያዩ ባንኮች ለተቋማችን ብድር አለመፍቀዳቸው

### 2.3.2. ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- በክልሉ ባጋጠመው የጸጥታ ችግር ምክንያት ያጋጠመውን የብድር ገንዘብ እጥረት ለመቅረፍ ከክልሉ ውጪ አዲስ አበባ ከተማ ላይ አንድ ቅርንጫፍ በመክፈት ሥራ ለመስራት ተሞክሯል።
- የብድር ገንዘብ እጥረትን ለመቅረፍ እና ቁጠባን ለማበረታታት ከፍተኛ የቁጠባ ወለድ በመስጠት እና የተለያዩ የቁጠባ አማራጮችን ለህብረተሰቡ በመስጠት ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል።

የተቋሙ ባለአክሲዮኖች በተመቻቸው የቁጠባ አማራጮች ተጠቃሚ በመሆን እና ሌሎችንም በመጋበዝ ከጎናችን እንድትሆኑ የጣና ማይክሮ ፋይናንስ ቦርድ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪውን ያስተላልፋል።

### 2.3.4. ለዳይሬክተሮች ቦርድ እና ለዋና ሥራ አስፈጻሚ የተደረጉ ክፍያዎች

ለእያንዳንዱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል እና ለዋና ሥራ አስፈጻሚ የተከፈለ አጠቃላይ የድካም ዋጋ የዓይነት ጥቅም የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና ካለበዓመታዊ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በቀረበው ሪፖርት ውስጥ መካተት እንዳለበት አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 314 ይደነግጋል፡በዚሁም መሰረት በ2024/2025 በጀት ዓመት በእያንዳንዱ የቦርድ አባል እና ለዋና ሥራ አስፈጻሚ የተከፈሉ የድካም ዋጋ እና ጥቅማ ጥቅሞች ቀጥሎ በተመለከተው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም ከነአያት | ኃላፊነት | የተካፋይ መጠን | | ጥቅማ ጥቅም | የብድር ዋስትና | ሌሎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በየወሩ | በዓመት | | | |
| 1 | አቶ ይልቃል ሞኘ ብዙነህ | የቦርድ ሰብሳቢ | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 2 | አቶ ስመኝ ካሴ እንደሻው | ም/ቦርድ ሰብሳቢ | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 3 | አቶ ደረጀ ምትኩ ጣሰው | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 4 | አቶ አለበል አታለል ቸኮል | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 5 | አቶ አበበ ልየው አንተነህ | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 6 | አቶመርኃጽድቅ መኮንን አባይነህ | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 7 | ወ/ሮ ንግስት ብዙአየሁ | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |

ጣና ማይክሮ ፋይናንስ TMFI Tana Micro F

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አቶ መልካሙ ውበት ገሠሠ | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 9 | አቶ ኃይሌ ገ/ዮሐንስ ጭሮም | አባል | የለም | 70,959.00 | የለም | የለም | የለም |
| 10 | አቶ እንደለ ማርቆስ ሰንዳቦ | ዋ/ሥራአስፈጻሚ | 104,193 | | | | 8,000 |

### 3. የ2018 በጀት የካምፓኒው ዋና ዋና ተግባራት

በ2018 በጀት ዓመት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ለብድር አገልግሎት የሚውል በጀት ተይዟል።

- በዚህ መሰረት ከቁጠባ ብር 113 ሚሊዮን፣ከብድር ተመላሽ ብር 131 ሚሊዮን ከአክሲዮን ሽያጭ ብር 30 ሚሊዮን ከባንክ ብድር ብር 30 ሚሊዮን ብር እና ከተሰራጨ ብድር ወለድ ገቢና ተዛማጅ የገቢ አይነቶች ብር 79.4 ሚሊዮን በድምሩ 383.4 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ እና ለብድር አገልግሎት ለማዋል በእቅድ ተይዟል።
- በ2018 በጀት ዓመት ለ984 ተበዳሪዎች ብር 281.7 ሚሊዮን ብር በማሰራጨት፣ ዓመታዊ ገቢን ወደ ብር 79.4 ሚሊዮን በማሳደግ እና ከታክስ በፊት ብር 22.3 ሚሊዮን ለማትረፍ በእቅድ የተያዘ ሲሆን፣ ለቁጠባ ወለድ ወጪና ሌሎች መደበኛ ወጪዎች ብር 57.1 ሚሊዮን ወጪ ይወጣል ተብሎ ታቅዷል።
- የ2018 በጀት ዓመት አጠቃላይ የብድር ተመላሽ (Loan Repayment) ወደ ብር 131 ሚሊዮን ለማድረስ እቅድ ተይዟል።
- በበጀት ዓመቱ 4 አዲስ ቅርንጫፎችን በመክፈት የቅርንጫፎችን ቁጥር 13 ለማድረስ እቅድ ተይዟል።
- በ2018 በጀት ዓመት ተቋሙን በከፍተኛ ደረጃ በማስተዋወቅ 6 ሺህ አክሲዮን እያንዳንዳቸው በ5 ሺህ ብር ስሌት፣ በድምሩ 30 ሚሊዮን ብር በመሸጥ ካፒታልን ከማሳደግ በተጨማሪ ለተቋሙ መደበኛ ተግባራት ማስፈጸሚያ የሚዉል ገንዘብ ለማግኘት በእቅድ ተይዟል።
- በበጀት ዓመቱ የተቋሙን የፋይናንስ ስርዓት በኮር ባንኪንግ አሰራር አጠናክሮ በማስቀጠል ለመስራት በእቅድ ተይዟል።
- በያዝነው በጀት ዓመት 3 የቁጠባ እና 2 የብድር አቅርቦት አይነቶችን በአዲስ ለተቋሙ ደንበኞች ለማቅረብ ዕቅድ ተይዟል።

በመጨረሻም እነዚህን እቅዶች ከግብ ለማድረስ ከባለህብቱ እና ከአክሲዮን አባሎቻችን ከፍተኛ ድጋፍ የሚያስፈልገን በመሆኑ፣ ይህንኑ አውቃችሁ ከወዲሁ ከፍተኛ እገዛ እንድታደርጉልን በራሴና በቦርዱ ስም ጥሪዬን እያቀረብኩ፣ በዚሁ አጋጣሚ የተቋሙን የሥራ አመራር ቦርድ፣ ማኔጅመንቱን እና ሰራተኞቹን እንዲሁም ባለአክሲዮኖቻችና መላ ደንበኞቻችን በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ላሳዩት ትጋት ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!!